በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
የኢጣሊያና አካባቢው (ኢጣሊያ፣ፈረንሳይ፣ ቤልጂየም፣
ቱርክ፣ ስፔይን እና ማልታ) ሀገረ ስብከት ጽ/ ቤት

The Ethiopian Orthodox Tewahedo Church
in Italy and The Surrounding (Italy, France, Belgium,
Turkey, Spain, and Malta) Diocese Secretariat

ሐምሌ ፲፪ ቀን ፳፻፲፭ ዓ/ም

**ወቅታዊ የቤተ ክርስቲያናችንን ችግር አስመልክቶ ከኢጣሊያ እና አካባቢው ሀገረ ስብከት የተሰጠ የአቋም መግለጫ**

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን የኢጣሊያ እና አካባቢው ሀገረ ስብከት ዓመታዊ ጠቅላላ መንፈዊ ጉባዔውን ሐምሌ ፲፩ እና ፲፪ ቀን ፳፻፲፭ ዓ/ም በፈረንሳይ ልዮን ደብረ ብሥራት ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን አካሂዷል። ጉባዔው የ፳፻፲፭ ዓ/ም የሀገረ ስብከቱን እና የአጥቢያ አብያተ ክርስቲያናትን የሥራ ክንውንና የሂሳብ ሪፖርት አዳምጧል። የቀጣይ ዓመት እቅዶችንም ገምግሞ አጽድቋል።

ከሀገረ ስብከት ጽ/ቤት እና ከእየ አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት በቀረቡት ሪፖርቶችና የ፳፻፲፮ ዓ/ም የበጀት ዓመት እቅዶች ላይ በሰፊው ተወያይቷል። በወቅታዊ የቤተ ክርስቲያናችን ፈተናዎች ላይም ጊዜ ወስዶ በጥልቀት መክሯል። የሚከተለውንም የአቋም መግለጫ አውጥቷል።

1. ሐምሌ ፱ ቀን ፳፻፲፭ ዓ/ም ቅዱስ ሲኖዶስ የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንትን እና የምእመናንን ጥያቄ ወደ ጎን በመተው ቀኖና ቤተ ክርስቲያንንም ባልጠበቀ ሁኔታ የፈጸመው በተለይም ለበርካታ አህጉረ ስብከት መሰበርና መዘረፍ ለካህናትና ምእመናን ሞትና ስደት ቁስለኛነትና ሥራ አጥነት ምክንያት የሆኑትንም ያካተተው ሲመተ ኤጲስቆጶሳት በእጅጉ ያሳዘነን መሆኑን እየገለጽን ይህ ሕገ ቤተ ክርስቲያንን ወደጎን የገፋ የኤጲስቆጶሳት አሿሿም መዘዙ ብዙ ስለሆነ እንዳይደገም በጥብቅ እናሳስባለን።
2. ሐምሌ 9 ቀን ፳፻፲፭ ዓ/ም በተፈጸመው ቀኖና በተ ክርስቲያንን ያልጠበቀ ሥርዓተ ሲመት ብናዝንና ብንከፋም የቤተ ክርስቲያናችንን ሕጓን እና ሥርዓቷን ጠብቆ ለሚወርድ የቅዱስ ሲኖዶስ ውሳኔ ተፈጻሚነት የበኩላችንን ለመወጣት ዝግጁ መሆናችንን እንገልጻለን።
3. በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል በትግራይ የተወሰኑ ጳጳሳት አንዲት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያናችንን ለመክፈልና ቀኖና ቤተ ክርስቲያንን በጣሰ መልኩ ለመፈጸም የሚያደርጉትን የሲመተ ኤጲስቆጶሳት እንቅሳቃሴ ነገ እንደ እሳት የሚያቃጥል ፀፀትን የሚያስከትልባቸው መሆኑን እንዲያስተውሉና እንዲያቆሙ አጥብቀን እንጠይቃለን የሚያደርጉትም ከሆነ በጥፅኑዕ እንቃወማለን
4. መንግሥት ተቀዳሚ ተግባሩ ሕግ ማስከበር እስከሆነ ድረስ በሕገ ወጥ መንገድ የቤተ ክርስቲያንን ሕጋዊ ሰውነት የሚዳፈሩትን ሥርዓት እንዲያስይዝልን እንጠይቃለን።
5. በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሥር የሰደደውን የፖለቲካ ጣልቃ ገብነት ፣ ሲሞናዊ እና ዘረኛ አሠራር በቃል ከማውገዝ ባለፈ በተግባር የሚወገዝበት እና ከቤተ ክርስቲያን ተነቅሎ የሚወጣበትን መንፈሳዊ አሠራር በመዘርጋት በቀጣይ ሊመጡ ከሚያሠጉ ችግሮች ቤተ ክርስቲያንን እንዲታደግ ቅዱስ ሲኖዶስን አጥብቀን እንጠይቃለን።
6. ቅዱስ ሲኖዶስ ሊቃውንቱን እና ምዕመናኑን የማወያየት እና የማሳተፍ ልምድ እንዲኖረው እንጠይቃለን።
7. ቅዱስ ሲኖዶስ ችግሮች ከመከሠታቸው እና ጉዳት ከማድረሳቸው አስቀድሞ የመከላከል ስልቶችን እንዲከተል እናሳስባለን።

እግዚአብሔር አምላካችን ቤተ ክርስቲያናችንን እና ሀገራችን ኢትዮጵያን ከክፉ ሁሉ ይጠብቅልን።

አባ ሕርያቆስ
Abba Heryacos
Archbishop of Italy and the Surrounding Diocese and Head of M/Kidusan St. Gabriel & Abune Teklehaimanot Church Oslo Norway

Maria dehlis vei 27B, 1084, Oslo Norway + 47 463 06 684 ahyesus@gmail.com
Via Castelpizzuto no. 21, 00131 Roma + 393501328030 secretary@eotcit.org